# *የሙያ ደኅንነትና ጤንነት ኮሚቴ ስለሚቋቋምበት ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 834/2014*

*2014ዓ.ም*

*አዲስአበባ*

# መመሪያ ቁጥር 834/2014

## የሙያ ደኅንነትና ጤንነት ኮሚቴ ስለሚቋቋምበት ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ

**መግቢያ**

በድርጅት ደረጃ የሥራ ላይ አደጋዎችና የጤና ጉዳቶች ለመከላከል ለመቆጣጠርና በዚህ ሳቢያ የሚከሰቱ ሰብአዊ ኢኮኖሚያዊ ማኀበራዊና ስነልቦናዊ ጉዳቶችን ለመቀነስ ይቻል ዘንድ ከአሠሪና ከሠራተኛ የተወከሉ የሁለትዮሽ የሙያ ደህንነትና ጤንነት ኮሚቴ ማቋቋምና ተግባርና ኃላፊነታቸውን ለመወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ይህ መመሪያ ወጥቷል፡፡

1. **አውጭው ባለሥልጣን**

   የሠራተኛና ማኀበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 171/1 (ኀ) መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

2. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ "የሙያ ደኅንነትና ጤንነት ኮሚቴ ስለሚቋቋምበት ሁኔታ ለመወሰን የወጣ የወጣ መመሪያ ቁጥር 834/2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

3. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፦

   1. **"አዋጅ"** ማለት የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 ማለት ነው፡፡
   2. **"የሙያ ደህንነትና ጤንነት አጠባባቅ"** ማለት በመከላከል መርህ ላይ የተመሰረተ፣ የሥራ ቦታዎች ምቹ፣ ጤናማና ከአደጋ የተጠበቁ እንዲሆኑ ለማድረግ፣ ጤናማ አምራች ዜጋ ለመፍጠርና የሥራ ውጤትና ምርታማነት ለማሳደግ የሚያስችል የተደራጀ፣ በሥርዓት የሚመራና በቅንጅት የሚፈጸም የልማት እንቅስቃሴ ነው፡፡
   3. **"የሙያ ደኅንነትና ጤንነት ኮሚቴ"** ማለት ከአሠሪ እና ከሠራተኞች በተወከሉ አካላት የሚቋቋምና በድርጅት ደረጃ የሙያ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅን ተቋማዊ ተልእኮ ገቢራዊ የማድረግ ኃላፊነት የተሰጠው የሁለትዮሽ ኮሚቴ ነው፡፡
   4. **"የአደጋ ተከላካይ ሠራተኛ"** ማለት በድርጅት ደረጃ ሠራተኞች የሚሰሩት ሥራ ሊያስከትልባቸው ስለሚችለው አደጋና በጤንነት ላይ ስለሚደርስ ጉዳት ለመከላከል የሚያስችሉ ተቋማዊ የጥንቃቄ እርምጃዎች ይወሰዱ ዘንድ የዕለት ከዕለት ክትትል እያደረገ የማሻሻያ አስተያየት የሚሰጥና ሲፈቀድም አተገባበሩን የሚከታተል በአሠሪው የሚመደብ ባለሙያ ነው፡፡

5. በአዋጁ አንቀፅ 2 ሥር የተመለከቱት ትርጓሜዎች ለዚህ መመሪያ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡
6. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ፆታ ይጨምራል፡፡

## 4. የተፈፃሚነት ወሰን

1. ይህ መመሪያ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 በሚሸፈኑና ቁጥራቸው 10 እና ከ10 በላይ የሆኑ ሠራተኞች ተቀጥረው በሚሠሩበት ድርጅት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
2. ከላይ በተራ ቁጥር 4.1 የተጠቀሰው አንቀፅ ቢኖርም ከ10 በታች የሠራተኛ ቁጥር ያላቸውና በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ በሚሸፈኑ ድርጅቶች በጋራ በመሆን የሙያ ደህንነትና ጤንነት ከሚቴ ሊያቋቁሙ ይችላሉ፡፡
3. ከድርጅቶች ተቋማዊ አደረጃጀትና የሥራ ባህሪ አኳያ ተጠሪነታቸው ለዋናው ድርጅት ሆኖ በቅርንጫፍ ደረጃ ተመሳሳይ ተልእኮ ለመፈፀም የተቋቋሙ ድርጅቶች ራሱን የቻለና ከዋናው የሙያ ደህንነትና ጤንነት ጋር በተጣጣመ መልኩ አደረጃጀት ሊፈጥሩ ይችላሉ፡፡

## 5. የሙያ ደህንነትና ጤንነት ኮሚቴ ስለማቋቋም

1. ማንኛውም አሠሪ በሥራ ቦታ የሠራተኞችን ደህንነትና ጤንነት በሚገባ ለመጠበቅና ምቹ የሥራ አካባቢ ለመፍጠር እንዲቻል የሙያ ደህንነትና ጤንነት ኮሚቴ ያቋቁማል፡፡
2. የኮሚቴው ተጠሪነት ለድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ይሆናል፡፡
3. የሙያ ደህንነትና ጤንነት ኮሚቴ ቁጥራቸው እኩል የሆኑ አሠሪውን እና ሠራተኞችን የሚወክሉ አባላት ያሉት ሆኖ
   ሀ. ቁጥራቸው ከ10 እስከ 100 የሆኑ ሠራተኞች ተቀጥረው በሚሰሩበት የሥራ ቦታ ከእያንዳንዳቸው ሁለት ተወካይ
   ለ. ቁጥራቸው ከ101 እስከ 500 የሆኑ ሠራተኞች ተቀጥረው በሚሰሩበት የሥራ ቦታ ከእያንዳንዳቸው አራት ተወካይ
   ሐ. ቁጥራቸው ከ501 እስከ 1000 የሆኑ ሠራተኞች ተቀጥረው በሚሰሩበት የሥራ ቦታ ከእያንዳንዳቸው ስድስት ተወካይ
   መ. ቁጥራቸው ከ1001 በላይ የሆኑ ሠራተኞች ተቀጥረው በሚሰሩበት የሥራ ቦታ ከእያንዳንዳቸው ስምንት ተወካይ ይኖሩታል፡፡
4. የኮሚቴው አደረጃጀት ለሴቶች ተሳትፎ ትኩረት የሰጠ ሊሆን ይገባል፡፡

5. ኮሚቴው የራሱ የሆነ የአሠራር ሥርዓት አዘጋጅቶ በማፅደቅ ተግባራዊ ሊያደርግ ይችላል፡፡

6. **የሙያ ደህንነትና ጤንነት ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት**

ኮሚቴው የሚከተሉት ተግባርና ሀላፊነቶች ይኖሩታል፦

1. በየዓመቱ የሙያ ደኅንነት ጤንነትና የሥራ አካባቢ መደበኛ የሥራ እቅድና በጀት በማዘጋጀት በድርጅቱ ሲፀድቅ በሥራ ላይ የማዋል፤
2. ቢያንስ በሦስት ወር አንድ ጊዜ የሥራ ቦታ መደበኛ የሙያ ደኅንነት፣ ጤንነትና የሥራ አካባቢ ቁጥጥር በማድረግ መሻሻልና መስተካከል የሚገባቸውን የሥራ ሁኔታዎች የተመለከተ ምክረ ሀሳብ ያቀርባል፣ አፈፃፀሙንም የማስተባበር፣
3. በሥራ ቦታ ልዩ ክትትል የሚያስፈልጋቸውን የሥራ ላይ ጠንቆች፣ የአሠራር ዘዴዎችና ማሽኖችን በመለየት ተገቢው የደህንነት ፍተሻ እንዲደረግባቸው አስተያየት የማቅረብ፣
4. የሙያ ደኅንነት፣ ጤንነትና የሥራ አካባቢ በተመለከተ አሠሪውን እና ሠራተኞችን በማማከር ተከታታይነት ያላቸው የማሻሻያ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ግንዛቤ የማዳበር እና የሴፍቲ ባህል እንዲጎለብት በጥናት የተደገፈ ምክረ ሃሳብ የማቅረብ፣
5. በሥራ ላይ የደረሱ አደጋዎች እና የጤና ጉዳቶች ብዛት፣ ዓይነት እንዲሁም በእነዚህ ሳቢያ የወጡ የሕክምና ወጪዎች የባከኑ የሥራ ሰዓቶች፣ ለካሣ ክፍያ የወጡ ወጪዎች የተመለከቱ መረጃዎች በመሰብሰብና በማጠናከር በአደጋ ሳቢያ የደረሱ ኢኮኖሚያዊ ጉዳቶችን ሁኔታ የመተንተን፡፡
6. በሥራ ቦታ ስለተከሰቱ ወይም ሊከሰቱ ሰለነበሩ አደጋዎችና የጤና ጉዳቶች መንስኤ በመመርመር የአደጋውን መነሻ ምክንያት ለይቶ ችግሩ በድጋሚ እንዳይከሰት የሚያስችል ተጨባጭ እርምጃ እንዲወሰድ ለአሠሪው አስተያየት የማቅረብ፡፡
7. ከሠራተኞች ደኅንነት፣ ጤንነት እና የማኅበራዊ አገልግሎቶች ጋር ተያይዘው በሥራ ቦታ የሚነሱ ቅሬታዎችን በየወቅቱ በመመርመርና በማጥናት ተግባራዊ ሊደረጉ የሚገቡ መፍትሔዎችን ያካተተ ጥናታዊ ሪፖርት ማዘጋጀትና ለአሠሪው የማቅረብ፣
8. በሥራ ቦታ ስለተወሰዱ ወይም እየተወሰዱ ስላሉ አጠቃላይ የአደጋ እና የጤና ጉዳት መከላከያ እርምጃዎች ብቃት አሠሪውን ያማክራል፤
9. በሥራ ቦታዎች የሙያ ደኅንነት ጤንነት፣ የሥራ አካባቢ አጠባበቅ አስመልክቶ የሥራ ላይ አደጋን ስለመከላከል የትምህርትና ሥልጠና ኘሮግራሞች እንዲዘጋጁ

ሃሳብ ማቅረብ፣ ፕሮግራም ያዘጋጃል፣ የፕሮግራሙን አፈፃፀም ውጤታማነት ይገመግማል፤

10. የሥራ ላይ አደጋዎችንና የጤና ጉዳቶችን ለመከላከል ለመቀነስ በግልም ሆነ በቡድን በሠራተኞች የሚደረጉ ጥረቶችንና የፈጠራ ሥራዎችን ያበረታታል፣
11. የሙያ ደኅንነት ጤንነትና የሥራ አካባቢ አጠባበቅን በተመለከተ በማኔጅመንቱ እና በሠራተኞች መካከል ቀልጣፋ እና ትክክለኛ የሴፍ መረጃዎችን ልውውጥ አሠራር መዘርጋትና ትምህርታዊ መድርኮችና የውይይት ፎርሞች ያዘጋጃል፤
12. በሥራ ቦታዎች የሙያ ደኅንነትና ጤንነት ቀን በተለያዩ ትምህርታዊ ፕሮግራሞች ተከብሮ እንዲውልና በዚህም ወቅት በአርአያነት የሚጠቀሱ የሥራ ክፍሎች፣ ሠራተኞች እና ሥራዎቻቸው እውቅና እንዲያገኙ በማድረግ በጎ የውድድር መንፈስ ይፈጥራል፤
13. በጥናት ላይ ተመስርቶ የድርጅቱን የሙያ ደኅንነትና ጤንነት ፖሊሲና ፕሮግራም መቅረፅ፣ ሲፀድቅም ተፈፃሚ የማድረግና አፈፃፀሙን የመከታተል፣ ውጤታማነት በመገምገም የማሻሻያ ሃሣብ ያቀርባል፤
14. አግባብ ካላቸው አካላት በመቀናጀት የህፃናት ጉልበት ብዝበዛን እና ኤች.አይ.ቪ /ኤድስን በሥራ ቦታዎች የመከላከል ቀንን በትምህርታዊ ፕሮግራም ማክበር
15. በሥራ ቦታዎች የሙያ ደኅንነትና ጤንነት ጠንቆችንና የሥራ ላይ አደጋዎችን ለመከላከል የሚረዱ ትምህርታዊ ጽሁፎች፣ ብሮሸሮች፣ ፖስተሮች፣እንዲሁም የጥንቃቄ መመሪያዎች ወዘተ እንዲለጠፉ ማድረግ፤
16. ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን የሚመድባቸው የሥራ ሁኔታ ተቆጣጣሪዎች ሥራቸውን በአግባቡ እንዲያከናውኑ ተገቢውን ድጋፍ መስጠት፤
17. በሥራ ቦታዎች ላይ የሚደርሱ ጉዳቶችን ወይም አደጋዎችን መረጃ በየጊዜው መዝግቦ መያዝ፤ የአደጋ ሁኔታ ቀላልና ጊዜያዊ ጉዳይ ያስከተለ ከሆነ በየሩብ አመቱ፣ አደጋው ከባድና ከፍተኛ የንብረት ውድመት ያደረሰ ከሆነ በአፋጣኝ ሚኒስቴሩ እና አግባብ ላለው ባለስልጣን ሪፖረት ያቀርባል፤
18. በሥራ ቦታዎች የሚካሄዱ የሙያ ደህንነት ጤንነትና አጠባበቅ ፕሮግራሞች ለሴቶች፣ ለወጣት ሠራተኞች ለአካልና ጉዳተኞች፣ ቫይረሱ በደማቸው ላለባቸው ሠራተኞች ትኩረት በመስጠት አስፈላጊውን ድጋፍና እገዛ እንዲያገኙ ማድረግ፣
19. ሴት ሠራተኞች በሥራ ቦታ ከሚደርስባቸወ ወሲባዊ ጥቃትና ትንኮሳ የተጠበቁ እንዲሆኑ የሚያስችሉ ተጨባጭ ሥራዎችን ያከናውናል፣

20. በሥራ ቦታዎች የኮቪድ 19 ወረርሽኝ የመከላከል ሥራን አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ይሰራል፣
21. አህጉራዊ እና አለማቀፋዊ ወረርሽኝ ሲከሰት በስራ ቦታዎች የመከላከል ሥራ አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ይሠራል፣
22. ለሠራተኞች የሚሰጡ የነፍስ ወከፍ አደጋ መከላከያ የመሣሪያዎችና አልባሳት ተገቢነት ያላቸው መሆናቸውንና በአግባቡ ሥራ ላይ መዋላቸውን ክትትል በማድረግ የማሻሻያ አስተያየት ያቀርባል፣
23. በድርጅቱ የሙያ ደኅንነትና ጤንነትን አጠባበቅን ለማጠናከር የአካባቢ ጥበቃና የክሊነር ፕሮዳክሽን አሰራሮች እንዲዘረጉ ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር ይሰራል፣
24. የድርጅቱን አደጋ የመከላከል አቅም ሊያሳድጉ የሚችሉ ሌሎች ተያያዥ ተግባራትን ያከናውናል፣

7. **የሙያ ደህንነት ጤንነት ኮሚቴ አባላት አመራረጥ**

1. አሠሪ በድርጅቱ በአመራር ላይ ካሉ  የማኔጅመንት አካላት  መካከል አሠሪን በመወከል የኮሚቴ አባል እንዲሆኑ ይመርጣል፤
2 በማኅበር የተደራጁ ሠራተኞች በማኅበራቸው አማካኝነት ሰራተኛን የሚወክሉ የኮሚቴ አባላትን ይመርጣሉ፤
3 በማኅበር ያልተደራጁ ሠራተኞች ባሉበት ድርጅት የጠቅላላ ሠራተኛ ብዛት በድምፅ ብልጫ የሚመረጡ ሠራተኞችን ለአባልነት  ይመርጣሉ፤
4 ከአንድ በላይ ማኅበር በተቋቋመበት ድርጅት ማኅበራቱ በጋራ በመሆን የኮሚቴ አባላቱን በድምፅ ብልጫ ይመርጣሉ
5 የሙያ ደህንነትና ጤንነት ኮሚቴ ተልዕኮ በቀጣይነት ለመተግበር ይቻል ዘንድ አሠሪ እና ሠራተኞች እንደ አስፈላጊነቱ ከእያንዳንዳቸው ሁለት ተጠባባቂ አባላትን በመምረጥ የኮሚቴው አባላት ሲጓደሉ እንዲተኩ ያደርጋሉ፡፡
6 የኮሚቴ አባላት አመራረጥ የተለያዩ የሥራ ክፍሎች እና የሥራ ባህሪን ያማከለ ሊሆን ይገባል፡፡
7 አሰሪው ለተመራጭ ኮሚቴ አባላት የተመራጭነት ደብዳቤ ይሰጣል፡፡

8 **የኮሚቴው አባላት የሥራ ዘመን**

1. የኮሚቴ አባላት የሥራ ዘመን ሦስት ዓመት ይሆናል፡፡
2. የኮሚቴው አባል ከአንድ የሥራ ዘመን በላይ ሊመረጥ ይችላል፡፡

3. የምርጫ ጊዜውን ያልጨረሰ የኮሚቴ አባል በሌላ አባል መተካት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ኮሚቴው ከተተኪዎች መካከል አባል እንዲሆን በድምፅ ብልጫ ይመርጣሉ፡፡

9 **የኮሚቴ አባላት ስልጠና**

1. እያንዳንዱ የኮሚቴ አባል በተመረጡ ሁለት ወር ጊዜ ውስጥ መሠረታዊ የሙያ ደኅንነትና ጤንነት ሥልጠና እንዲያገኙ ድርጅቱ ተገቢውን ጥረት ያደርጋል፡፡
2. የኮሚቴው አባል ቀደም ሲል ሥልጠና የወሰደ ከሆነ ተጨማሪ ሥልጠና ሳያስፈልገው አባል ሆኖ ሊቀጥል ይችላል፡፡

10 **የኮሚቴው ሰብሳቢ እና ምክትል ሰብሳቢ አመራረጥ**

1. ከአሠሪ እና ከሠራተኛ ተወካዮች መካከል በየዓመቱ በየተራ ሰብሳቢ እና ምክትል ሰብሳቢ ሆነው የሚያገለግሉ ኮሚቴው ይመርጣል፡፡
2. የስብሳቢ እና የምክትል ሰብሳቢው አመራረጥ እና ስለሚቀያየሩበት ሁኔታ ኮሚቴው በሚያወጣው የአሠራር ሥርዓት መሠረት የሚወሰን ይሆናል፡፡

11. **<u>የኮሚቴው የስብሰባ ጊዜ</u>**

1. ኮሚቴው በተቋቋመ በሠላሳ ቀናት ውስጥ የመጀመሪያ ስብሰባውን ያደርጋል፡፡
2. ኮሚቴው ቢያንስ በሶስት ወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፡፡
3. ከላይ በተራ ቁጥር ሁለት የተመለከተው ቢኖርም በሥራ ቦታ ከባድ አደጋ ወይም አደገኛ ሁኔታ ወይም አሳሳቢ የጤና ችግር ሲከሰት ወይም መከሰቱ ሲያሰጋ የሙያ ደህንነትና ጤነነት ኮሚቴው አስቸኳይ ስብሰባ ሊያካሂድ ይችላል፡፡
4. ማናቸውም የኮሚቴ የስብሰባ ጊዜ በአሠሪው የተፈቀደና በመደበኛ የሥራ ሰዓት የሚካሄድ ይሆናል፡፡

12. **<u>ምልዕተ ጉባኤ</u>**

1. ከኮሚቴው አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ የስብሰባው ምልዐተ ጉባዔ እንደተሟላ ይቆጠራል፣
2. ከላይ በተራ ቀ. 1 የተመለከተው ቢኖርም በስብሰባው ከአሠሪ እና ከሠራተኞች ተወካዮች ቢያንስ ግማሽ ከተገኙ ምላተ ጉበኤው እንደተገኘ ይቆጠራል

3. ኮሜቴው ወሳኔ የሚያሳልፈው በስምምነት ይሆናል፣ ስምምነት ባልተደረሰ ጊዜ በተገኙት አባላት የድምጽ ብልጫ ይሆናል፤ ድምፅ እኩል ለእኩል በተከፈለ ጊዜ የሰብሳቢወን የድጋፍ ድምጽ ያገኘው የወሳኔ ሀሳብ ይጸድቃል፤

4. ኮሚቴው በአጀንዳ ከሚነጋገርባቸው ጉዳዮች ጋር ቅርበት ያላቸውን ባለሙያዎች በኮሚቴው ስብሰባ ላይ በአስረጂነት ሊጋብዝ ይችላል፡፡

13. የኮሚቴው ቃለ ጉባኤ

1. የኮሚቴው ቃለ ጉባኤዎች በስብሰባው ላይ በተገኙ አባሎች ይፈረማሉ፣
2. የኮሚቴው ስብሰባ እንደተጠናቀቀ በኮሚቴውን የተፈረመ ቃለ ጉባዔ ቅጅ በሰብሳቢ በኩል ለአሠሪው እና ለእያንዳንዱ የኮሚቴ አባል እንዲደርስ ያደርጋል፡፡
3. የኮሚቴው ቃለ ጉባዔ ዶክመንት ተደርጎ በሙያ ደህንነትና ጤንነት ኮሚቴ ጽ/ቤት እንዲቀመጥ ይደረጋል፡፡
4. የድርጅቱ የሙያ ደህንነትና ጤንነት ባለሙያ፣ በድርጅቱ የተቋቋመ የሙያ ደህንነትና ጤንነት ኮሚቴ አባላት፣ የሥራ ሁኔታ ተቆጣጣሪ ወይም አግባብ ያለው አካል ሲጠይቅ ቃለ ጉባኤ መመልከት ይችላል፡፡

14. የኮሚቴው ሰብሳቢ ተግባር እና ሀላፊነት

1. የኮሚቴውን ስብሰባ ይመራል፣ ኮሚቴው ሥራውን በእቅዱና በፕሮግራሙ መሠረት ማከናወኑን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ይገመግማል፡፡
2. የኮሚቴው አባላት የድርጅቱን የሙያ ደኅንነትና ጤንነት ፖሊሲና ፕርግራም እንዲያውቁ ያደርጋል፡፡
3. የሥራ ላይ አደጋዎችን ለመከላከል በግል ወይም በቡድን የሚደረጉ ጥረቶችን ያስተባብራል፣ ለጥረቶቹ ተገቢው ድጋፍና እገዛ እንዲሰጥ ያደርጋል፡፡
4. የኮሚቴው አባላት የተሠጣቸውን ኃላፊነት በአግባቡ መወጣታቸውን ይከታተላል ይቆጣጠራል፡፡
5. በተለያዩ ምክንያቶች በሚጓደሉ የኮሚቴው አባላት ምትክ ከተጠባባቂዎች መካከል በወቅቱ እንዲተኩ ያደርጋል፡፡
6. በኮሚቴ በኩል የሚቀመጡ የማሻሻያ ምክረ ሀሳቦች ተግባራዊ መደረግ አለመደረጋቸውን ይከታተላል፡፡
7. አሠሪውና ኮሚቴው ወቅታዊ የጋራ የምክክር መድረኮች እንዲኖራቸው ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡

15. የኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ ተግባርና ሀላፊነት

ምክትል ሰብሳቢ:-

1. ሰብሳቢው በማይኖርበት ጊዜ ሰብሳቢዉን ተክቶ ይሰራል፤
2. በኮሚቴው የሚሰጡት ሌሎች ተግባራት ይፈጽማል::

## 16. የኮሚቴው ፀሐፊ ተግባርና ኃላፊነት

1. በድርጅቱ የተመደበ የአደጋ ተከላካይ ባለሙያ የኮሚቴው ቋሚ ፀሐፊ በመሆን ያገለግላል፡፡
2. የኮሚቴውን የስብሰባ አጀንዳ፣ የጉብኝትና የስራ ቦታ ቁጥጥር ኘሮግራም ከኮሚቴው ሰብሳቢዎች ጋር በመመካከር ያዘጋጃል፡፡
3. የኮሚቴውን ዶክመንቶችና መረጃዎች ያደራጃል፣ይይዛል፡፡
4. የኮሚቴውን ዓመታዊና ወርሃዊ የሥራ እቅድና መርሃግብር በማዘጋጀት በኮሚቴው ያፀድቃል፡፡
5. የሙያ ደኅንነትና ጤንነት መረጃዎችን ለአባላት ያሠራጫል፣
6. የኮሚቴው የሥራ ሪፖርቶች፣ ከሥራ ሁኔታ ተቆጣጣሪ የሚተላለፉ መመሪያዎች እና የመሳሰሉት ለኮሚቴው መቅረባቸውን ያረጋግጣል የተሰጡ አቅጣጫዎች ተግባራዊ መደረጋቸውን ይከታተላል ሪፖርት ያደርጋል፡፡
7. የሙያ ደኅንነትና ጤንነት ኘሮግራሞችን ያስተባብራል፡፡
8. የሥራ ላይ አደጋዎች፣ የጤና መታወኮች እና ሌሎች የሙያ ደኅንነትና ጤንነትን የተመለከቱ መረጃዎች በወቅቱ ይመዘግባል ይተነትናል መረጃዎችን በማጠናቀር ለኮሚቴው ውይይት እና የውሣኔ ያቀርባል፡፡

## 17. ሌሎች የኮሚቴው አባላት ተግባርና ኃላፊነት

1. በኮሚቴው ስብሰባዎች ላይ ይገኛሉ፣ አስተያየት ይሰጣሉ፣ ውሣኔዎችን ያስተላልፋሉ፡፡
2. በየሥራ ክፍላቸው የሙያ ደኅንነትና ጤንነት ደረጃዎች መሟላታቸውን ይከታተላሉ፡፡
3. በድርጅቱ ውስጥ የሙያ ደኅንነትና ጤንነት አገልግሎትን ለማሣደግ ስለሚያስችሉ እርምጃዎች ሃሣብ ያመነጫሉ፡፡
4. በሥራ ቦታ በሚደረጉ ቁጥጥሮች፣ ምርመራዎች…ወ.ዘ.ተ ይሣተፋሉ፡፡
5. የሙያ ደኅንነትና ጤንነትን እና ማኅበራዊ አገልግሎትን በሥራ ቦታ ለማሣደግ የሚያስችሉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናሉ፡፡

6. በኮሚቴው ስብሰባ ላይ የተነሱ የሙያ ደኅንነትና ጤንነት ጉዳዮችን በተመለከተ ለሥራ ክፍላቸው አስተያየት ያቀርባሉ፡፡

18. የአሠሪው ኃላፊነት

1. የጽሕፈት መሣሪያዎች ፣ አመቺ የሆነ የመሰብሰቢያ ቦታ፣ እና ፀሐፊ ይመድባል፣ ሌሎች አስፈላጊ ሁኔታዎችን ያሟላል፡፡
2. የኮሚቴው አባላት በኮሚቴው ስብሰባዎች እና በሌሎች የኮሚቴው የሥራ እንቅስቃሴዎች እንዲሣተፉ ፈቃድ ይሠጣል፡፡
3. የኮሚቴው አባላት የሙያ ደኅንነትና ጤንነት ሥልጠና እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡
4. የሥራ ላይ አደጋዎች፣ አደገኛ ክስተቶች ወይም የጤና ጉዳቶች በተመለከተ የተጠናከሩ ጥናታዊ ሪፖርቶች እና ሌሎች ጠቃሚ መረጃዎች ጨምሮ የሙያ ደህንነትና ጤነትን አጠባበቅን የተመለከቱ ሰነዶች ለኮሚቴው ያቀርባል፡፡
5. ግልጽ የሆነ የሙያ ደኅንነትና ጤንነት ፖሊሲ በማፅደቅ ተግባራዊ እንዲሆን አመራር ይሰጣል፡፡የፖሊሲውን ቅጅ ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ላለው ባለስልጣን ይልካል፣
6. የድርጅቱን የሙያ ደኅንነትና ጤንነት ፕሮግራም እና የማስፈፀሚያ በጀት በማፅደቅ ተግባራዊ እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡
7. የሙያ ደኅንነትና ጤንነትን የተመለከቱ ሕጎችን እና መመሪያዎችን ለኮሚቴው ሥራ እንዲያገለግሉ ያደርጋል፡፡
8. የኮሚቴው ስብሰባዎች ቃለ ጉባዔ እና የሥራ ሪፖርቶች ሪከርድ በአግባቡ እንዲያዝ ያደርጋል፣
9. የሥራ ሁኔታዎች ምቹና ከአደጋ የተጠበቁ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኮሚቴው በሥራ ቦታዎች ቁጥጥር እንዲደረግ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ የቁጥጥሩን ውጤት በከፍተኛ የማኔጅመንት አካላት ደረጃ በመገምገም ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡
10. በሥራ ቦታዎች ለሴቶች፣ ወጣት ሠራተኞች ፣ ቫይረሱ በደማቸው ያለባቸው ወገኖችና አካል ጉዳተኞች ትኩረት በመስጠት አስፈላጊውን እገዛ እና ድጋፍ እንዲሰጥ ያደርጋል፡፡
11. ሴት ሠራተኞች በሥራ ቦታ ከሚደርስባቸው ፆታዊ ጥቃት ትንኮሳ ለመጠበቅ የሚያስችሉ አሠራሮች እንዲዘረጉና ተግባራዊ እንዲሆኑ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡

19. የሠራተኞች ኃላፊነት

1.በድርጅት ደረጃ የሙ-ያ ደህንነትና ጤንነት ፖሊሲዎች፣ መመሪያዎች ሲዘጋጁና የህብረት ድርድሮች ሲካሄዱ በንቃት መሳተፍ እና አስተ,ያየት መስጠት

2. የድርጅቱን የሴፍቲ ፖሊሲ ማክበር፣

3. ከኮሚቴው ጋር ተባብሮ መሥራት፣

4.በኮሚቴው ለሠራተኞች የሚሰጡ ሥራዎችን በኃላፊነት ስሜት በትብብር ማከናወን፣

4. ኮሚቴው የሰጣቸውን የጥንቃቄ መመሪያዎችና አስተ,ያየቶች ማክበር፣

5. በሥራ ላይ የሚያጋጥሟቸውንና ለአደጋ መከሰት ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ የአሠራር ስህተቶች ትክክለኛ ያልሆኑ የሥራ ተዋረዶች እንዲስተካከሉ የመፍትሔ ሃሳብ ማቅረብ ለተፈፃሚነቱም በባለቤትነት ስሜት መንቀሳቀስ፣

6. ሴት ሰራተኞች በሥራ ቦታ ከሚደርስባቸው ፆታዊ ጥቃት እና ትንኮሳ እንዲጠበቁ ተገቢውን ጥረት ማድረግ፡፡

20. ስለ መመዝገብ

1. በድርጅት ደረጃ የሚቋቋም የሙ-ያ ደህንነት ጤንነት ኮሚቴ በሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ባለው ባለስልጣን ተመዝግቦ ለአንድ አመት የሚያገለግል የምስክር ወረቀት ይሠጠዋል፡፡

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተሰጠው የምስክር ወረቀት በየዓመቱ ሊታደስ ይገባል፡፡

3. ኮሚቴው ለምዝገባ ሲቀርብ የአባላቱን ዝርዝር፣ የወከሉትን አካል እና በኮሚቴው ያላቸውን የሥራ ኃላፊነት፣ እንዲሁም ኮሚቴው የተመሠረተበትን ቃለ ጉባዔ ማቅረብ አለበት፣

4. ኮሚቴው የአባላት ለውጥ ሲያደርግ ሁኔታውን ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ላለው ባለስልጣን ማሣወቅ አለበት፣

‹

21. ስለ ሪፖርት አቀራረብ

1. ኮሚቴው የሥራውን እንቅስቃሴ በተመለከተ በየሶስት ወሩ የመጨረሻ ሰምንት ለአሠሪው ሪፖርት ያቀርባል፡፡

2. ኮሚቴው የሥራውን ክንውን በተመለከተ በየሶስት ወሩ የመጨረሻ ሰምንት ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ላለው ባለስልጣን ሪፖርት ያቀርባል፡፡

3. ኮሚቴው በድርጅቱ የተከሰቱ አደጋዎችና የደረሱ ጉዳቶች መኖር አለመኖራቸውን የሚገልፅ የአደጋ ሪፖርት በየወሩ የመጨረሻ ሳምንት ለአሠሪው እና ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ላለው ባለስልጣን ሪፖርት ያቀርባል፡፡

22. ስለ ተጠሪነት

የኮሚቴው ተጠሪነት ለአሰሪው ወይም ለድርጅቱ ዋና ስራአስኪያጅ ነው፡፡

23.የመተባበር ግዴታ

በዚህ መመሪያ ውስጥ በተደነገጉት ጉዳዮች ላይ ማናቸውም አካል የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

24. ስለ ቅጣት

በዚህ መመሪያ የተደነገጉትን የተላለፈ ማንኛውም ወገን በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 ስለ ቅጣት የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆኑበታል፡፡

25. መመሪያውን ስለማሻሻል

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የዚህን መመሪያ አፈፃፀም በየወቅቱ እየገመገመ ሊያሻሽል ይችላል፡፡

26. የተሻረ መመሪያ

የሙያ ደህንነት ጤንነት ኮሚቴ አቋቋምን ለመወሰን ከመስከረም 30 ቀን 1998 ዓ.ም. ጀምሮ የወጣው መመሪያ ተሽሯል፡፡

27. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በሚኒስትር ከተፈረመበት ቀን……………………../ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ

ኤርጎጌ ተስፋዬ (ዶ/ር)

የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር